# የከተማ ቤቶች ልማት ኤጀንሲ (MDHA)

# ተከራዮች: መብቶችዎን ይወቁ!

## በMDHA የሕዝብ ቤቶች የኔ ግዴታዎች ምንድን ናቸው?

- **በየዓመቱ እና የቤተሰብዎ መጠን ወይም ገቢዎ በሚቀየርበት ጊዜ በድጋሚ ያረጋግጡ። የቤተሰብዎን የገቢ መጠን ማረጋገጫ ለቤቱ ባለቤት ይስጡ።**
- **ኪራይዎን በየወሩ ይክፈሉ።** ገቢዎ ከተለወጠ ለንብረቱ ባለቤት ይንገሩ። በኪራይዎ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል!
- አስፈላጊውን ስምምነት እና የማረጋገጫ ቅጾችን **ይፈርሙ።**
- የኪራይ ውልዎን **አይጣሱ።** አደገኛ እና አስጊ የሆነ ነገር አያድርጉ። **ይህ የእርስዎን እንግዶችም ያካትታል።**
- የሚፈልጉት ጥገና ካለ ለአከራይዎ **በጽሁፍ** ወድያውኑ **ያሳውቁ።**

## MDHA ሊያስወጣኝ መሞከር የሚችለው መቼ ?

**MDHA እርስዎን ማስወጣት ወይም የኪራይ ውልዎን አለማደስን ሊመርጥ የሚችለው በምክንያት (በተለየ ምክንያት) ብቻ ነው።**ለምሳሌ፣ እርስዎ የሚከተሉትን ካደረጉ ቤትዎን ሊያጡ ይችላሉ።

- የገቢ ለውጦችን ካላሳወቁ ወይም ከእርስዎ ጋር ስለሚኖሩ ሰዎች ለባለንብረቱ ካልተናገሩ።
- የቤት ኪራይ ካልከፈሉ ወይም በተደጋጋሚ የቤት ኪራይ አዘግይተው የሚከፍሉ ከሆነ።
- ቦታውን ጤናማ ያልሆነ ወይም አስጊ እንዲሆን ካደረጉ.
- አደገኛ ወይም ህገወጥ የሆነ ነገር ማስፈራራት/አድርገው ከሆነ

## MDHA ሊያስወጣኝ የሚሞክር ከሆነ ምን ይፈጠራል?

- **ኪራይ ካልከፈሉ** ለመክፈል **የ14 ቀን ማስታወቂያ** ይደርስዎታል።
- **ማንኛውንም ሌላ ችግር** ለማስተካከል **የ30 ቀን ማስታወቂያ** ይደርስዎታል። ችግሩን ለመፍታት በ 30 ቀናት ውስጥ ከባለንብረቱ ጋር ለመገናኘት መጠየቅ ይችላሉ።
- በ14 ቀናት ውስጥ ኪራይ ካልከፈሉ ወይም ችግሩን በ30 ቀናት ውስጥ ካላስተካከሉ፣ **የፍርድ ቤት መጥሪያ ይደርስዎታል።**

**በወንጀል ድርጊት ወይም ሌሎችን በማስፈራራት ከተከሰሱ የሚደርስዎት ማስታወቂያ የአጭር ጊዜ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ስብሰባ መጠየቅ ላይፈቀድልዎት ይችላል።**

**የፍርድ ቤት መጥሪያ ከደረስዎት ወደ ፍርድ ቤት ይሂዱ! ካልሆነ በቀላሉ ይሸነፋሉ።**

## በMDHA የሕዝብ ቤት ፕሮግራም ያሉኝ ሌሎች መብቶች ምንድን ናቸው?

| | | | |
|---|---|---|---|
| ያዘገዩበት ቅጣት ክፍያዎ **ከኪራይዎ 10%** መብለጥ አይችልም። አንዳንድ የቅጣት ክፍያዎች **ከ$10** በላይ ሊሆኑ አይችሉም። የኪራይ ውልዎን ይመልከቱ! | የዘገየ ክፍያ **ስላለብዎት ብቻ** ከቤት መባረር አይችሉም። | የንብረቱ ባለቤት በተመጣጣኝ ጊዜ ውስጥ **አስፈላጊውን ጥገና** ማድረግ አለበት። | የንብረት አስተዳዳሪው የጋራ ቦታዎችን እና መገልገያዎችን **በአስተማማኝ እና ንጹህ ሁኔታ** ውስጥ ማስቀመጥ አለበት። |

AMHARIC - MDHA

LEGAL AID SOCIETY (833) 837-HOME

NHBA (615) 701-7957

AMAC (615) 988-6460

NASHVILLE CONFLICT RESOLUTION CENTER

ROOFTOP NASHVILLE

ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ካውንቲ ብቻ ነው። እዚህ የቀረበው መረጃ የህግ ምክር አይደለም ወይም የህግ ምክር ለመመስጠት የታሰበ አይደለም። የሕግ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለግል ጠበቃዎ ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የመካከለኛው ቴነሲ የሕግ ድጋፍ ማህበር እና የኩምበርላንድን ቢሮ በ1-800-238-1443 ይደውሉ ወይም የናሽቪል ሂስፓኒክ ባር ማህበር በ1-615-701-7957 ይደውሉ። 5/24 ተሻሽሏል።